በርግጥም ስለ ትልቅ ጉዳይ ነው የጠየቅከኝ፤ ጉዳዩ አላህ በርሱ ላይ ላቀለለለት ሰው ቀላል ነው።

ከሙዓዝ ቢን ጀበል - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አለ: «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ጀነት የሚያስገባኝንና ከእሳት የሚያርቀኝን ስራ ይንገሩኝ። አልኳቸው። እርሳቸውም: "በርግጥም ስለ ትልቅ ጉዳይ ነው የጠየቅከኝ፤ ጉዳዩ አላህ በርሱ ላይ ላቀለለለት ሰው ቀላል ነው። አላህን ልትገዛና በርሱ ላይ ምንንም ላታጋራ፤ ሶላትን ቀጥ ልታደርግ (በአግባቡ ልትሰግድ)፤ ዘካን ልትሰጥ፤ ረመዳንን ልትጾም፤ የአላህንም ቤት ሐጅ ልታደርግ ነው።" አሉና ቀጥለውም እንዲህ አሉ: "የመልካም ነገሮችን በር አልጠቁምህምን? ጾም ጋሻ ነው፤ ውሃ እሳትን እንደሚያጠፋው ሁሉ ምፅዋትም ወንጀልን ታጠፋለች፤ የሰውዬው በሌሊቱ አጋማሽ የሚሰግደው ሶላት" አሉና ቀጥለው {ጎኖቻቸው ከመጋደሚያ ስፍራዎች ይራራቃሉ} ከሚለው {ይሰሩትም በነበሩት} እስከሚለው ድረስ [ሱረቱ ሰጅዳ: 16‐17] አነበቡ። ቀጥለውም "የነገሩ ሁሉ ራስ፣ ምሰሶውንና ሻኛውን ልንገርህን?" አሉ። እኔም "እንዴታ የአላህ መልክተኛ ሆይ!" አልኳቸው። እርሳቸውም "የነገሮች ሁሉ ራስ (ዋና) እስልምና ነው፤ ምሰሶው ሶላት ነው፤ ሻኛው ጂሃድ ነው።" አሉ። ቀጥለውም "ይህን ሁሉ የሚቆጣጠረውን ነገር ልንገርህን?" አሉ። እኔም "እንዴታ የአላህ ነቢይ ሆይ!" አልኳቸው። ምላሳቸውን
ያዙና "በራስህ ላይ ይህቺን ቆጥባት!" አሉ። እኔም "የአላህ ነቢይ ሆይ! እኛ በምንናገረው እንያዛለንን?" አልኳቸው። እርሳቸውም "እናትህ ትጣህና ሙዓዝ ሆይ! ምላሳቸው ያጨደችው ካልሆነ በቀር ሰዎችን በፊታቸው ወይም በአፍጢማቸው እሳት ውስጥ የሚደፋቸው (ሌላ
ነገር) አለ እንዴ?" አሉኝ።»
[ሶሒሕ ነው።] [ቲርሚዚ ዘግበውታል።]

ሙዓዝ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ: ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጋር ጉዞ ላይ ነበርኩ። አንድ እለት እየተጓዝን ሳለ ወደርሳቸው ቀረብ አልኩኝና እንዲህ አልኳቸው: የአላህ መልክተኛ ሆይ! ጀነት የሚያስገባኝና ከእሳትም የሚያርቀኝን ስራ ይንገሩኝ። እርሳቸውም እንዲህ አሉ: በነፍስ ላይ መስራቱ ከባድ ስለሆነ ስራ ነው የጠየቅከኝ። አላህ በርሱ ላይ ላቀለለለት ግን ገርና ቀላል ነው። የእስልምናን ግዴታዎች ፈፅም: የመጀመሪያው: አላህን በብቸኝነት መገዛትና በርሱም አንዳችን አታጋራ፤ ሁለተኛው: በቀንና ምሽት አምስቱን ግዴታ ሶላቶች: ፈጅር፣ ዙህር፣ ዐስር፣ መግሪብና ዒሻን መስፈርታቸውን፣ ማዕዘናቸውንና ግዴታዎቻቸውን አሟልተህ ቀጥ አድርገህ መስገድ ነው፤ ሶስተኛው: ግዴታ የሆነብህን ዘካ ማውጣት ነው: ይህም ገንዘብ በሸሪዓ የተገደበን መጠን በደረሰ ጊዜ ለሚገባው አካል የሚሰጥ በሁሉም ገንዘብ ላይ ግዴታ የሆነ ገንዘባዊ አምልኮ ነው፤ አራተኛው: ረመዳንን ትጾማለህ: እርሱም አምልኮን በመነየት ጎህ ከወጣችበት ወቅት ጀምሮ ፀሐይ እስክትገባ ድረስ ከመብላት፣ ከመጠጣትና ከሌሎችም የሚያስፈጥሩ ነገሮችም መቆጠብ ነው። አምስተኛው: የሐጅ አምልኮን ለመተግበር አላህን ለማምለክ መካን በማሰብ የአላህን ቤት ሐጅ ማድረግ ነው። ቀጥለውም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: ወደ መልካም በሮች የሚያደርስ መንገድ አላሳውቅህምን? ይህም እነዚህን ግዴታዎችና ሱና ተግባራትን በመከተል ነው: የመጀመሪያው: ሱና ጾም መጾም ነው። ይህም ስሜትን በመስበርና ሀይልን በማድከም ወንጀል ላይ ከመውደቅ የሚከላከል ነው። ሁለተኛው: ሰደቃ (ግዴታ ያልሆነ ምፅዋት) መስጠት ነው። ይህም ወንጀል ከተሰራ በኋላ ወንጀልን ታጠፋለች፣ ታስወግዳታለች፣ ፋናዋንም ታብሳታለች። ሶስተኛው: በሌሊቱ የመጨረሻ ሲሶ የተሀጁድ ሶላት መስገድ ነው። ቀጥለው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) {ጎኖቻቸው ከመጋደሚያ ስፍራዎች ይራራቃሉ} በሶላት፣ በዚክር፣ በመቅራትና በዱዓ {ጌታቸውን ይጠሩታል።} {ለመፍራትና ለመከጀል ከሰጠናቸውም (ጸጋ) ይለግሳሉ። ከዓይኖች መርጊያ ለእነርሱ የተደበቀላቸውን (ጸጋ) ማንኛይቱም ነፍስ አታውቅም።} ማለትም የትንሳኤ ቀን በጀነት ውስጥ በሚያገኙት ፀጋ አይኖቻቸው በርሱ የምትረጋበትን ነፍሳቸው አታውቅም። {ይሰሩትም በነበሩት ለመመንዳት።} ቀጥለው ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ አሉ: የሃይማኖቱ መሰረት የሆነውን አልነግርህምን? መሰረቱ በርሱ ላይ የሚደገፍበት ምሰሶውንስ አልነግርህምን? ሻኛውንስ አልነግርህምን? ሙዓዝም (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - "እንዴታ የአላህ መልክተኛ ሆይ!" አለ። ነቢዩም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና: የነገሮች ራስ (ዋና) እስልምና ነው። እርሱም ሁለቱ የምስክር ቃላቶች ናቸው። የሃይማኖቱ መሰረት ከሰውዬው ጋር የሚቆይለት በሁለቱ ቃላት ነው። ምሰሶው: ሶላት ነው። ቤት ያለምሰሶ እንደማይኖር ሁሉ ያለ ሶላትም እስልምና የለም።

[illegible]

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/66530

النجاة الخيرية
ALNAJAT CHARITY

لجنة الدعوة الإلكترونية
EDC
E-Da'wah Committee